በ2015 የት/ት ዘመን የስልጤ ዞን ትምህርት መምሪያ የግል ት/ቤቶች የ6ኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ ዞናዊ ፈተና።

የተሰጠው ሰዓት 1:30

መመሪያ፡- ከ1-60 ለተሰጡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ መርጣችሁ በተሰጠው መልስ መስጫ ላይ ጻፉ/አጥቁሩ።

1. የተለያዩ የመሬት ክፍሎችና የውሃ አካላትን መነሻ በማድረግ ተረጋግጦ የሚገለጽ መገኛ የሆነው የቱ ነው?
   (A) አንጻራዊ መገኛ (C) የሎንግትዩድ መገኛ
   (B) የላቲቲዩድ መገኛ (D) ፍጹማዊ መገኛ
2. የአንድ ቦታ ፍጹማዊ መገኛን ለይቶ ለማወቅ ምን ጊዜም ቢሆን ቀድመን መፈለግ ያለብን የሀሳብ መስመር
   (A) ሎንግቱድ (B) የምድር ወገብ (C) ላቲትዩድ (D) ፕራይም ሜሪዲያን
3. የምድርን የሰሜን ዋልታ እና የደቡብ ዋልታ የሚያገናኝ የሀሳብ መስመር የቱ ነው?
   (A) ላቲትዩድ (B) ሎንግትዩድ (C) አንጻራዊ መገኛ (D) ፕራይም ሜሪዲያን
4. የሎንግትዩድ መስመሮች የሚገናኙት በምድር _____ ንፍቀ ክበብ ነው።
   (A) ምስራቅ እና ምዕራብ (C) ምስራቅ እና ደቡብ
   (B) ደቡብ እና ሰሜን (D) ምዕራብ እና ደቡብ
5. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል በምስራቅ አፍሪካ የሚዋሰኑት የትኞቹ ናቸው?
   (A) ቀይ ባህር እና ህንድ ውቅያኖስ (C) አባይ ወንዝ እና ቀይ ባህር
   (B) ታንጋኒካ እና ቪክቶሪያ ሀይቅ (D) ህንድ ውቅያኖስ እና ቪክቶሪያ ሀይቅ
6. በምስራቅ አፍሪካ ከሚገኙ ሀገሮች መካከል አነስተኛ የህዝብ ብዛት ያለው የቱ ነው?
   (A) ኢትዮጵያ (B) ኬኒያ (C) ሲሼልስ (D) ጁቡቲ
7. በምስራቅ አፍሪካ ከሚገኙ ደሴቶች መካከል በስፋት ከሌሎች የሚበልጠው የቱ ነው?
   (A) ሲሼልስ (B) ሪዩኒዮን (C) ኮሞሮስ (D) ማዳጋስካር
8. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል አንዱ በካርታ አይወከልም።
   (A) የፖለቲካ ድንበር (B) የመኪና እቃዎች (C) የመሬት ክፍሎች (D) መንገድ
9. ከሚከተሉት ውስጥ የጂፒኤስ አካል **ያልሆነው** የቱ ነው?
   (A) የህዋ ሳተላይት (B) የመሬት መገናኛ (C) መገልገያ እቃዎች (D) ሰላማዊነት
10. የአፍሪካ ቀንድ በሚባለው የምስራቅ አፍሪካ ክልል ውስጥ **የማይገኘው** የቱ ነው?
    (A) ኢትዮጵያ (B) ሶማልያ (C) ኡጋንዳ (D) ኤርትራ
11. በምስራቅ አፍሪከ ከሚገኙ ደሴቶች መካከል የማይመደበው የቱ ነው?
    (A) ጁቡቲ (B) ሲሼልስ (C) ኮሞሮስ (D) ማዳጋስከር
12. ከሁሉም የደም አይነቶች ደም መቀበል የሚችለው የደም አይነት የቱ ነው?
    (A) A (B) B (C) AB (D) O
13. በሰውነታችን አደጋ ሲደርስ የሚፈሰውን ደም ለመቀነስ ወይም እንዲረጋ የሚያደርገው የቱ ነው? (A) ነጭ የደም ሴል (B) ፕሌትሌት (C) ቀይ የደም ሴል (D) ፕላዝማ

14.የአንድ ጤናማ ሰው የልብ ምት በደቂቃ ምን ያህል ነው?

(A) ከ40 - 100 (B) ከ20 - 100 (C) ከ50 - 100 (D) ከ60 -100

15.በሴት ልጅ ለአቅመ ሄዋን መድረስ ወቅት ከሚታዩ ለውጦች የማይመደበው የቱ ነው?

(A) የዳሌ መስፋት (C) የጡት ማደግ

(B) ድምጽ መጎርነን (D) የብብት እና የሀፍረተ ስጋ አካባ ጸጉር መብቀል

16.በወንድ ወይንም በሴት ልጆች ላይ በአይን፣ በምላስም ሆነ በሌላ መንገድ የሚደረግ ተገቢ ያልሆነ እንቅስቃሴ ምን ተብሎ ይጠራል?

(A) ጭውውት (B) ማሽኮርመም (C) ጸታዊ ትንኮሳ (D) ጥል

17. አየር በውስጡ ከሚይዛቸው ነገሮች ውስጥ የማይመደበው የቱ ነው?

(A) ኦክሲጂን (B) ወርቅ (C) ካርቦንዳይኦክሳይድ (D) ናይትሮጂን

18.አየር ወደውጭ በምናስወጣበት ወቅት የሚፈጠረው የተ ነው?

(A) ድልሺ(ዲያፍራም) ይሰፋል (C) የጎድን አጥንት ከፍ ይላል

(B) (ድልሺ)ዲያፍራም ይሰበሰባል (D) ጡንቻ ይላላል

19.በጎድን አጥንት መሃል የሚገኘው ጡንቻ ምን ተብሎ ይጠራል?

(A) ድልሺ (B) ሳምባ (C) ኢንተርኮስታል ጡንቻ (D) ትራክያ

20.ከሚከተሉት የድብልቅ አይነቶች መካከል በአይን መለየት የማንችለው ድብልቅ የቱ ነው?

(A) ውሃ እና ዘይት (B) ጋዝ እና ውሃ (C) አሻዋ እና ስኳር (D) ውሃ እና ስኳር

21.ከተጠቀምንባቸው በኋላ መልሰን ልናገኛቸው የምንችላቸው የሀይል ምንጮች ምን በመባል ይታወቃሉ?

(A) ታዳሽ የሀይል ምንጮች (C) የተፈጥሮ ጋዝ

(B) ታዳሽ ያልሆኑ የሀይል ምጮች (D) የነዳጅ ዘይት

22. ከዚህ በታች ከተሰጡት ቀላል ማሽኖች ውስጥ እንጨት ለመፍለጥ፣ለመክፈል እና ለመሰንጠቅ የሚያገለግለው የቱ ነው? (A) ብሎን (B) ሽብልቅ (C) ፑሊ (D) ሊቨር

23. ከእንጨት እና ከብረት የሚዘጋጅ እና የማስደገፊያ ቦታውን (ፈልክረም) በማቀያየር በመጠቀም ክብደት ለማንሳት የሚያገለግል የቀላል ማሽን የቱ ነው?

(A) ፑሊ (B) ብሎን (C) ሊቨር (D) ሽብልቅ

24.ቡና ከቦቆሎ ቢደባለቅባችሁ በምን መንገድ መለየት ትችላላችሁ?

(A) በመውቀጥ (B) በማግኔት (C) በማዝቀጥ (D) በመልቀም

25. ውሃ ከጋዝ፣ ውሃ ከዘይት እና የተለያየ መጠነ ፍሌት ያላቸውን ፈሳሾች ለመለየት የትኛውን ዘዴ እንጠቀማለን? (A) ማግኔት (B) ማዝቀጥ (C) ማበጠር (D) ማትነን

26.የማይሟሙ ጠጠር ነገሮችን ከፈሳሽ ነገሮች በማጥለያ እቃ መለየት ምን በመባል ይታወቃል?

(A) ማጥለል (B) ማትነን (C) በማፍላት ማትነን (D) ማበጠር

27. በአየር ውስጥ ናይትሮጂን በመቶኛ የሚይዘው ድርሻ ስንት ነው?

(A) 20.9% (B) 0.9% (C) 78% (D) 1%

28. በምስራቅ አፍሪካ ከምድር ወገብ 6° ሰሜን እና 6° ደቡብ የሚገኘው የአየር ንብረት የቱ ነው?

(A) ሞይስት ትሮፒካል (B) ደረቅ ሀሩር (C) ኢካቶሪያል (D) ደረቅ ትሮፒካል

29.ከሚከተሉት አማራጮች መካከል መጠነ ሙቀትን አስመልክቶ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

(A) ሜርኩሪ ቴርሞ ሜትር ከፍተኛ ሙቀትን ለመለካት ያገለግላል

(B) አልኮል ቴርሞ ሜትር ዝቅተኛ ሙቀት ለመከላት ይውላል

(C) በዲግሪ ሴልሺየስ ሊገለጽ ይችላል (D) የአንድን ቁስ ብዛት ይወክላል

30. ከሚከተሉት ውስጥ የአየር ንብረት እንዲፈጠር መንስዔ የሚሆነው የቱ ነው?
(A) የአየር እርጥበት (B) አልቲቱዩድ (C) ንፋስ (D) ዳመና
31.በምስራቅ አፍሪካ ከሚገኙ ሀገሮች አማካይ የዝናብ መጠኑ 97ሚ.ሌ የሆነው የቱ ነው?
(A) ኢትዮጵያ (B) ኬንያ (C) ሲሼልስ (D) ታንዛኒያ
32.በምስራቅ አፍሪካ ከሚገኙ ሀገሮች ከፍተኛ የተከማቸ ወርቅ የሚገኝባት ሀገር የቷ ነች?
(A) ታንዛኒያ (B) ኬኒያ (C) ኢትዮቶጵያ (D) ኡጋንዳ
33.በምስራቅ አፍሪካ ለአፈር መሸርሸር መንስኤ ያልሆነው የቱ ነው?
(A) ንፋስ (B) ችግኝ መትከል (C) ሰር በከፍተኛ ሁኔታ ማስጋጥ (D) የደን መመንጠር
34.በኢትጵያ ከሚገኙ ሀይቆች በስፋቱ በአንደኛ ደረጃ የሚቀመጠው የትኛው ነው?
(A) ጣና ሀይቅ (B) ሀዋሳ ሀይቅ (C) ዝዋይ ሀይቅ (D) ላንጋኖ ሀይቅ
35.በኢትዮጵያ ከሚገኙ ሀይቆች መካከል በከፍተኛ ሁኔታ ጨው የሚመረትበት ሀይቅ ---------- ነው።
(A) ጣና (B) ዝዋይ (C) አፍዴራ (D) ላንጋኖ
36.በምስራቅ አፍሪከ ከሚገኙ ሀይቆች መካከል ትልቁ ሀይቅ የትኛው ነው?
(A) ታንጋኒካ (B) ጣና (C) ዝዋይ (D) ቢክቶሪያ
37.በምስራቅ አፍሪካ ከሚገኙ ዋና ዋና ወንዞች መካከል የማይጠቀሰው የቱ ነው?
(A) ጣና ወንዝ (B) አቲ ወንዝ (C) ጉሪቾ ወንዝ (D) ናይል ወንዝ
38. በምስራቅ አፍሪካ ከሚገኙ ሀይቆች መካከል በጥልቀቱ የመጀመሪያ ደረጃ የሚይዘው የቱ ነው?
(A) ታንጋኒካ (B) ሩደልፍ (C) ጣና (D) ቢክቶሪያ
39.በምስራቅ አፍሪካ ከሚገኙ የእጽዋት አይነቶች ያልሆነው የቱ ነው?
(A) የበረዷማ እጽዋት (C) የከፍተኛ ቦታዎች እጽዋት
(B) የምድር ወገብ አካባቢ እጽዋት (D) የሳር ምድር እጽዋት
40.ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ የአፈር አይነት ሆኖ ቀለል ያለ እና እርጥበት አዘል ሲሆን ምርታማ የአፈር አይነት ምን በመባል ይጠራል?
(A) የሸክላ አፈር (B) ድቡልቡል አፈር (C) ኖራ አፈር (D) ለም አፈር
41. የንፋስ ፍጥነት መለኪያ መሳሪያ ምን በመባ ይታወቃል?
(A) ዊንዲቬን (B) አኔሞ ሜትር (C) ሬንጌጅ (D) ባሮ ሜትር
42.የህዋ ወይም የአየር ግፊት መለኪያ ምን ተብሎ ይጠራል?
(A) ፓስካል (B) ዲግሪ ሴንቲግሬድ (C) ሰአት (D) ቴርሞ ሜትር
43.በምስራቅ አፍረካ ከሚገኙ ሀገሮች ከፍተኛ ሙቀት ያላት ሀገር የትኛዋ ናት?
(A) ኢትዮጵያ (B) ኬኒያ (C) ጁቡቲ (D) ታንዛኒያ
44.የጂቡቲ ዋና ከተማ ማን ናት? (A) ቪክቶሪየ (B) አዲስ አበባ (C) ናይሮቢ (D) ጂቡቲ
45.ከሚከተሉት ውስጥ በምስራቅ አፍሪካ ሰው ሰራሽ ቅርሶች መካከል የሚመደበው የቱ ነው?
(A) መስጂዶች (B) ወንዞች (C) ሀይቆች (D) ተራሮች
46. ከሚከተሉት ውስጥ የመሬት መዓድናትን አለአግባብ በመጠቀም ከሚመጡ ችግሮች መካከል ያልሆነው የቱ ነው?
(A) በመዓድን ስራ ወቅት የሚፈጠር አደጋ (C) የአካባቢ ችግሮች
(B) የመዕድናት በክፍተኛ ሁኔታ እና በፍጥነት መመናመን (D) የአካባቢ መዋብ
47. ከሚከተሉት መካካል በምስራቅ አፍሪካ ከሚገኙ እንስሳት መካካል የመይመደበው የቱ ነው?
(A) በመጥፋት ላይ ያለ ቀይ ቀበሮ (B) ባለ ጋማ እና ሸንተር ጅብ (C) የእርሻ በሬ (D) ቆርኪ

48. ከሚከተሉት የምስራቅ አፍሪካ የቱሪስት ቦታዎች ማጎ ፓርክ የሚገኘው የት ነው?
(A) ኬኒያ (B) ኢትዮጵያ (C) ሩዋንዳ (D) በኤርትራ

49.ከሚከተሉት በተፈጥሮ ከተገኙ ቅሪቶች ውስጥ ያልሆነው የቱ ነው?
(A) ቤተ መንግስቶች (B) የውሃ ፏፏቴዎች (C) ሀይቆች (D) የዱር እንስሳት

50.በምስራቅ አፍሪከ ከሚገኙ የቱሪስት ቦታዎች ውስጥ ማሳይ ማረ ፓርክ የሚገኘው በየትኛው ሀገር ነው?
(A) ታንዛኒያ (B) ኢትዮጵያ (C) ኬኒያ (D) ሩዋንዳ

51. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ አፈር ከምንከባከብባቸው መንገዶች የሚመደበው የቱ ነው?
(A) ሳር ጨርሶ ማስጋጥ (C) በንፋስ አቅጣጫ ማረስ
(B) የደን መመንጠር (D) ገላጣ በሆኑ ቦታዎች ችግኝ መትከል

52.ክብደት ያለው እና ካልሲየም ካርቦኔት በውስጡ የያዘ የአፈር አይነት የቱ ነው?
(A) የሸክላ አፈር (B) የኖራ አፈር (C) አሻዋማ አፈር (D) ለም አፈር

53.ኤች አይ ቪ ኤድስ ተብሎ የሚጠራው በሽታ የሚያጠቃው የትኛውን የደም አይነት ነው?
(A) ቀይ የደም ሴል (B) ፕሌትሌት (C) ነጭ የደም ሴል (D) ፕላዝማ

54.ከሚከተሉት ውስጥ የኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ ምልክት ያልሆነው የቱ ነው?
(A) ድካም (B) የጡንቻ መጠንከር (C) ራስ ምታት (D) አቅም መጣት

55.በሴት ልጅ ላይ የሚደረጉ ጎጂ ልማዳዊ ድርቶች ውስጥ የማይመደበው የቱ ነው?
(A) የሴት ልጅ ግርዛት (C) አስገድዶ መድፈር
(B) ህገ ወጥ ውርጃ (D) ሴቶችን ወደ ት/ቤት መላክ

56.ኤች አይቪ ኤድስ ከሰው ወደ ሰው ከሚተላለፍባቸው መንገዶች ውስጥ የማይመደበው የቱ ነው?
(A) አብሮ መብላት
(B) ቫይረሱ ካለባቸው ሰዎች ጋር ጥርስ መፋቂያ አብሮ መጠቀም
(C) ቨይረሱ ካለባቸው ሶዎች ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት መፍጠር
(D) ስለት ያላቸውን ነገሮች አብሮ መተቀም

57.በአፍሪካ ውስጥ በድርቅ በከፍተኛ ሁኔታ ከተጠቁ ሀገሮች የሚመደበው የትኛው ሀገር ነው?
(A) ኡጋንዳ (B) ሶማሊያ (C) ኤርትራ (D) ናይጀሪያ

58.የኤች አይቪ ኤድስ በሽታ በደማቸው ላለባቸው ሰዎች ማድረግ ያለብን ድጋፍ የቱ ነው?
(A) ማግለል (C) የተመጣጠነ ምግብ እንዲመገቡ ማድረግ
(B) ችላ ማለት (D) ምላጭ መዋዋስ

59.ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ድርቅ ለመከላከል ያገለግላል፡፡
(A) ችግኝ መትከል (C) በንፋስ አቅጣጫ ማረስ
(B) ደን መመንጠር (D) ችግኞችን አለመንከባከብ

60.የጤና ችግር ማለት ምን ማለት ነው?
(A) የሰውነት ክፍሎች የተፈጥሮ ባህሪ መቀየር (C) መጫወት
(B) ልዩ መነቃቃት (D) መተባበር